https://chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፯
አዲስ አበባ መጋቢት ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No. 27
ADDIS ABABA 24th March,2020

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፸፱/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

የሲቪል አቪዬሽን (ማሻሻያ) አዋጅ.....፲፪ሺ፫፻፵፮

**Content**

Proclamation No. 1179./2020

The Civil Aviation (Amendment) Proclamation ……..Page 12346

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፸፱/፪ሺ፲፪

## የሲቪል አቪዬሽን አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለስልጣን ሥር የነበረው የአውሮፕላን አደጋና አጋጣሚ ምርመራ ቢሮ ከዓለም አቀፍ የሲቪል አቪዬሽን ተቀጽላ ፲፫ እና በወቅታዊ ምክረ ሃሳብ አንፃር በመነሳት በገለልተኝነት ራሱን ችሎ በአዋጅ ቁጥር ፱፻፺፯/፪ሺ፭ መሰረት በመቋቋሙ፣

ከአቪዬሽን ኢንዱስትሪ ተለዋዋጭነት አንፃር የሲቪል አቬዬሽን አዋጅ ቁጥር ፮፻፲፯/፪ሺ፩ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

**፩· አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የሲቪል አቪዬሽን (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፸፱/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION No. 1179/2020

## A PROCLAMATRION TO PROVIDE FOR THE AMENDMENT OF CIVIL AVIATION PROCLAMATION

**WHEREAS,** the air craft accident and incident investigation bureau which used to be under Ethiopian Civil Aviation Authority has been established as a neutral body through Proclamation 957/2016 in accordance with the standards and recommended practices in Annex 13 of the convention on international civil aviation;

**WHEREAS**, it is required to amend Ethiopian Civil Aviation Proclamation No. 616/2008 in view of the dynamic nature of the aviation industry;

**NOW THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby Proclaimed as follows.

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "The Civil Aviation (Amendment) Proclamation No·1179/ 2020."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

https://chilot.me



**፪. <u>ማሻሻያ</u>**

የሲቪል አቪዬሽን አዋጅ ቁጥር ፮፻፲፮/፪ሺ፩ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል።

"፩/ "አደጋ" ማለት ማንኛውም ሰው በአውሮፕላን ለመሄድ በማሰብ በአውሮፕላን ከተሳፈረበት ጊዜ ጀምሮ ሁሉም ሰው እስከሚወርድበት ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ከአውሮፕላኑ እንቅስቃሴ ጋር ግንኙነት ያለው ሆኖ ወይም ሰው አልባ አውሮፕላን ከሆነ አውሮፕላኑ በረራን በማሰብ ለመንቀሳቀስ ከተዘጋጀበት ጊዜ ጀምሮ በበረራው መጨረሻ አውሮፕላኑ እስከሚያርፍበት እና ቀዳሚው የማንቀሳቀሻ ሲስተም እስከሚጠፋበት ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ፡-

ሀ) በተፈጥሮ ምክንያት ወይም በራሱ ወይም በሌሎች ሰዎች ድርጊት ምክንያት ወይም ለመንገደኞች ወይም ለአውሮፕላን ሠራተኞች ከሚገባ ቦታ ውጭ በድብቅ ሲጓዝ ከሚደርስበት ጉዳት በስተቀር፤

(፩) በአውሮፕላን ውስጥ በመሆኑ፤

(፪) ከአውሮፕላኑ አካል ወይም ከአውሮፕላኑ ከተገነጠሉ አካላት ጋር በቀጥታ በመነካካቱ፤ ወይም

(፫) አውሮፕላኑ በሚነሳበትና በሚያርፍበት ወቅት ወይም በመሬት ላይ እንቅስቃሴ በሚያደርግበት ወቅት ከሞተር ክፍሉ በሚያወጣው ከፍተኛ ፍጥነትና ሀይል ያለው የተቃጠለ አየር በቀጥታ በመጋለጡ፣ የሚያጋጥመው ከባድ የአካል ጉዳት ወይም ሞት፡፡

ለ) አውሮፕላኑ ጉዳት ደረሰበት ወይም አካላዊ ጥንካሬውን አጣ የሚባለው፡-

**2. <u>Amendment</u>**

The Civil Aviation Proclamation No. 616/2008 is here by amended as follows:

1/ Sub-Article (1) of Article 2 is deleted and replaced by the following new Sub-Article (1)

"1) "Accident" means an occurrence associated with the operation of an aircraft which, in the case of a manned aircraft, takes place between the time a person boards the aircraft with the intention of flight until such time as all such persons have disembarked, or in the case of an unmanned aircraft, takes place between the time the aircraft is ready to move with the purpose of flight until such time as it comes to rest at the end of the flight and the primary propulsion system is shutdown, in which:

a) except when the injuries are due to natural causes, self-inflicted or inflicted by acts of other persons, or when the injuries are to stowaways hiding outside the areas normally available to passengers and crew; a person is fatally or seriously injured as a result of:

(1) his being in the aircraft;

(2) his direct contact with the body or any part of the aircraft, including parts which have become detached from the aircraft; or

(3) his direct exposure to jet blast occurring from landing or takeoff or during taxi.

b) an aircraft is deemed to have sustained damage or structural failure when:

https://chilot.me



(፩) የአውሮፕላኑ አካላዊ ጥንካሬ፣ ብቃት ወይም የበረራ ባህሪያቱን በከፍተኛ ደረጃ ሲጎዳ፡፡

፪/ አውሮፕላኑ ሞተር መጥፋት፣ መጎዳት፣ ከፍተኛ ጥገና ወይም መተካት ሲያስፈልገው ሲሆን ነገር ግን ጉዳቱ በአንድ ሞተር ላይ ብቻ ሲሆን እና በሽፋኑ ወይም በተጓዳኝ ዲጋፊ፣ ኢጋኘ አካላት፣ በውልብልቢቶች፣ ክንፎቹ ጫፎች፣ በአንቴናዎች፣ ፕሮብስ፣ ቬንስ፣ ጎማዎች፣ ፍሬኖች፣ የጎማ መያዣ አቃፊዎች፣ የአውሮፕላን ፍጥነት ለመቀነስ ኢጋኘ መሣሪያዎች፣ ፓኔሎች፣ ላንዲንግ ጊር ዶርስ፣ የፊት መስታወት፣ የአውሮፕላኑ ሽፋን ላይ የሚታዩ (ትንንሽ መሰርጎዶች ወይም የተበሱ ቀዳዳዎች) ወይም በሄሊኮፕተር ከሆነ በሽክርክሪቱ ላይ የሚደርስ መጠነኛ ጉዳት፣ በጭራው ላይ በሚገኝ ሽክርክሪት ላይ የሚደርስ መጠነኛ ጉዳት፣ በሄሊኮፕተር ላይ ያለው ላንዲንግ ጊር እና ከጠጣር በረዶ ወይም ከወፍ ግጭት በአውሮፕላኑ ላይ የሚፈጠሩ ቀዳዳዎች ውጭ አውሮፕላኑ ላይ ከፍተኛ ጥገና ወይም የተጎዳውን አካል መተካት ሲያስፈልገው፡፡

(1) the structural strength, performance or flight characteristics of the aircraft is adversely affected.

2/ the aircraft would normally require major repair or replacement of the affected component, except when the damage is limited to a single engine including its cowlings or accessories, to propellers, wing tips, antennas, probes, vanes, tires, brakes, wheels, fairings, panels, landing gear doors, windscreens; the aircraft skin such as small dents or puncture holes, or for minor damages to main rotor blades, tail rotor blades, landing gear; and those resulting from hail or bird strike like holes in the Aircraft.

“ሐ) የአውሮፕላኑ መጥፋት ወይም ጨርሶ የማይደረስበት መሆን ነው።”

“c) the aircraft is missing or is completely inaccessible.”

፪/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተተክቷል።

2/ Sab-Article (3) of Article 2 is deleted and replace by the following new Sub-Article (3).

“፫) “የአውሮፕላን ማረፊያ” ማለት በመሬት ወይም በውሃ ላይ የተከለለ ቦታ ሆኖ በውስጡ ማንኛውንም ህንጻዎችን፣ የተዘረጉ መሰረተ ልማቶችን እና መሳሪያዎችን ጨምሮ በሙሉ ወይም በከፊል ለአውሮፕላን ማረፊያ፣ እና መንቀሳቀሻ የሚያገለግል ቦታ ነው፡፡”

“3/ “Aerodrome” means defined area on land or water including any buildings, installations and equipment intended to be used either wholly or in part for the arrival, departure and surface movement of aircraft.”

፫/ መነሻ የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተተክቷል።

3/ Sub-Article (5) of Article 2 is deleted and replaced by the following new Sub-Article (5).

“፭/ “አውሮፕላን” ማለት አየር ከመሬት ገጽታ ጋር ከሚያደርገው መስተጋብር ውጭ ከገዛ አካሉ ጋር በሚያደርገው ግጭት የተነሳ በከባቢ አየር ውስጥ ድጋፍ የሚያገኝ ማንኛውም በራሪ መሣሪያ ነው፡፡”

“5/ “Aircraft” means any machine that can derive support in the atmosphere from the reactions of the air with itself other than the reactions of the air against the earth’s surface.”

https://chilot.me



፬/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፮) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፮) ተተክቷል።

"፮/ "የአውሮፕላን ሞተር" ማለት ለአውሮፕላን ማንቀሳቀሻ በጥቅም ላይ የዋለ ወይም ሊውል የታሰበ ሆኖ ለሞተሩ ሥራና ቁጥጥር የሚያስፈልጉ ማናቸውም የዚሁ ክፍልና አካል የሚያጠቃልል ሲሆን ውልብልቢትን አይጨምርም፤"

4/ Sub-Article (6) of Article 2 is deleted and replaced by the following new Sub-Article (6).

"6/ "Aircraft Engine" means a unit used or intended to be used for aircraft propulsion which consists of at least those components and equipment necessary for functioning and control, but excludes the propeller or rotors when applicable."

፭/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፳፰) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፳፰) ተተክቷል።

"፳፰/ "ጠቅላላ አቪዬሽን ኦፕሬሽን" ማለት ከንግድ አየር ትራንስፖርትና ከኤሪያል ሥራ ውጭ የተለየ የአቪዬሽን ሥራ ማለት ነው።"

5/ Sub-Article (28) of Article 2 is deleted and replaced by the following new Sub-Article (28).

"28/ "General Aviation operation" means an aircraft operation other than commercial air transport or an aerial work operation."

፮/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፴፪) ድንጋጌ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፴፪) ተተክቷል፡፡

"፴፪/ "ኤሮድሮም ኦፕሬተር" ማለት አንድን የአየር ማረፊያ አቅዶና ገንብቶ አውሮፕላኖች እንዲያርፉበትና እንዲነሱበት የሚያመቻች አካል ነው፡፡"

6/ Sub-Article (32) of Article 2 is deleted and replaced by the following new Sub-Article (32)

"32/ "Aerodrome Operator" means any person, organization or enterprise engaged in planning, constructing and operation of an aerodrome.

፯/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፴፬) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፴፬) ተተክቷል።

"፴፬/ "የመለዋወጫ ዕቃ" ማለት የአውሮፕላን አካላትን ለመቀየር ወይም ለመጠገን የሚያገለግል ቁስ አካል ሲሆን የአውሮፕላን ሞተሮችን እና ውልብልቢቶችን ይጨምራል፤"

7/ Sub-Article (34) of Article 2 is deleted and replace by the following new Sub-Article (34)

"34/ "Spare Part" means a component used for the replacement or repair of aircraft bodies including engines and propellers."

፰/ ከአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፴፰) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፴፱) ተጨምሮ ከንዑስ አንቀጽ (፴፱ እስከ (፵፮) ያሉት እንደ ቅደም ተከተላቸው ከንዑስ አንቀጽ (፵) እስከ (፵፯) ሆነው ተሸጋሽገዋል:-

"፴፱/ "ቅኝት" ማለት ለአየር ትራፊክ ቁጥጥር ዓላማ የራዳርንና ሌሎች መሳሪያዎችን ተጠቅሞ አውሮፕላን ያለበትን ትክክለኛ ቦታ ማወቅ ማለት ነው፡፡

8/ The following new Sub-Article (39) is added after Sub-Article (38) of the Proclamation and the existing subsequent Sub-Articles (39) to (46)are renumbered as Sub-Articles (40) to (47):

"39/"Surveillance "means detecting the position of aircraft using radar and other detecting equipment(s) for the purpose of air traffic control.

https://chilot.me



፱/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፵፬) (እንደተሸጋሸገ) ተሰርዞ በሚከትለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፵፬) ተተክቷል፡፡

"፵፬/ "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የትራንስፖርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው።

፲/ የአዋጁ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተሰርዟል፡፡

፲፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፲ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) ተሰርዞ በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) ተተክተዋል።

"፫/ የአውሮፕላን ማረፊያዎችን ደህንነት ለማረጋገጥ:-

ሀ) የግንባታና ማስፋፊያ ሥራ ዲዛይን መርምሮ ያጸድቃል፡፡

ለ) የአውሮፕላን ማረፊያዎችን ይመረምራል፣ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ የሥራ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፡፡"

"፬/ በኢትዮጵያ አየር ክልል ውስጥና ከኢትዮጵያ አየር ክልል ውጭ የአየር ትራፊክ አገልግሎት፣ የመገናኛ ናቪጌሽንና ቅኝት አገልግሎት እንዲሁም የኤሮኖቲካል መረጃ አገልግሎት ይሰጣል፡፡"

፲፪/ የአዋጁ አንቀጽ ፲ ንዑስ አንቀጽ (፲፭) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፲፭) ተተክቷል።

"፲፭/ ለሚሰጠው የኤርናቪጌሽን አገልግሎት በዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ኮንቬሽንና መመሪያዎች መሰረት ተመን አውጥቶ ክፍያ ይሰበስባል እንዲሁም ለበረራ ደህንነት ምርመራ፣ ቁጥጥር እና ክትትል ተግባር እና ማናቸውም ሌሎች አገልግሎቶች ከአየር መንገዶች እና ከኤርፖርቶች የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያፀድቀው ተመን መሰረት ክፍያ ይሰበስባል፡፡"

፲፫/ ከአዋጁ አንቀጽ ፲ ንዑስ አንቀጽ (፲፮) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (፲፯ እስከ ፴፫) ተጨምረው ነባሮቹ ንዑስ አንቀጾች (፲፯) እስከ (፲፱) እንደቅደም ተከተላቸው ከንዑስ አንቀጽ (፴፬) እስከ (፴፮) ሆነው ተሸጋሽገዋል።

9/ Sub-Article (44) of article 2 as reshuffled is deleted and replaced by the following new Sub-Article (44).

"44/ "Ministry or Minister" means Ministry or Minister of Transport."

10/ Sub-Articles (3) of Article 3 is deleted.

11/ Sub-Articles (3) and (4) of Article 10 are deleted and replaced by the following new Sub-Articles (3) and (4).

"3/ To ensure airport safety & security:

a) Check and approve designs of aerodrome.

b) Inspect, certify, license and regulate aerodromes

"4/ Provide air traffic services, communication, navigation and surveillance services, and aeronautical information services within the Ethiopian airspace, and as deemed necessary outside Ethiopian airspace."

12/ Sub-Article (15) of Article 10 is deleted and replaced by the following new Sub-Article (15).

"15/ Collect fees and charges for Air Navigation services according to international civil aviation convention and rules; further collect fees and charges for flight safety, inspection, control and follow up any other services from operators and airports enterprise based on approved tariff by the Council of Ministers."

13/ The following new Sub-Articles (17 to 33) are added after Sub-Article (16) of Article 10; and Sub-Articles(17-19) of Article 10 are renumbered as Sub-Articles (34) to (36) respectively."

https://chilot.me



“፲፯/ በአየር ትራንስፖርት ዘርፍ በአደገኛ ቁሶች አጓጓዥነትና በላኪነት ሥራ ላይ ለተሰማሩ ሰዎች ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል።”

“17/ The Authority shall grant licenses to those individuals engaged in handling and forwarding of dangerous goods by air upon meeting the established criteria; renews and suspends license for good cause; and revokes the license that it granted wherever appropriate.”

“፲፰/ ከደንቦች፣ መመሪያዎችና ደረጃዎች አፈጻጸም ነፃ ስለማድረግ፦

ሀ) ኦፕሬተሩ ወይም የሥራ ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ወገን ወይም ከባለስልጣኑ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ወይም እንደ ሁኔታው የአቪዬሽን ተግባር ስልጣን የተቀበለ አካል ሲያመለክት በባለስልጣኑ የወጡ መመሪያዎችን፣ ትዕዛዞችን፣ ሥርዓቶችን ትግበራ አስመልክቶ ጠያቂው አማራጭ የአሰራር ዘዴ አዘጋጅቶ ሲያቀርብ ባለስልጣኑ ለተወሰነ ጊዜ ነፃ ሊያደርገው ይችላል። ነፃ የሚደረግበት ሁኔታ በባለስልጣኑ መመሪያ ይወሰናል።

ለ) ከላይ በፊደል ተራ (ሀ) መሰረት የተሰጠ ነፃ የመሆን መብት በማንኛውም መንገድ ከስድስት ወራት ያልበለጠ ሆኖ ጠያቂው ወይም አገልግሎት ሰጪው ከባለስልጣኑ መመሪያ ወይም አሰራር ሙሉ በሙሉ ነፃ የሚሆንበት እና ነፃ የመሆን መብቱ አብቅቶ መመሪያውን ወይም አሰራሩን ሙሉ ለሙሉ መከተል የሚጀምርበት ጊዜ በጽሑፍ ተገልጾ መሰጠት ይኖርበታል።”

“18/ Exemptions from Regulations, Directives and Standards:

a) The Authority may grant exemptions for a limited period of time upon an application by an operator, a licensee or a certificate holder or a holder of any authorization, as the case may be, with respect to application of any procedure, directives or order issued by the Authority provided that the applicant has put in place an alternative means of compliance thereof.

b) Exemptions granted in accordance with Paragraph (a) herein above shall be in writing specifying the time when the aviation service provider is expected to fully comply with the requirements of the Authority and the period within which the exemption shall cease to be effective, provided that the duration of any such exemption shall not exceed six months.”

“፲፱/ አግባብነት ባለው ህግ መሰረት ውክልና ሲሰጠው ከተለያዩ አገራትና የኤሮኖቲካል ባለስልጣናት ጋር የአየር አገልግሎት ስምምነቶችን ይደራደራል፣ ይፈራረማል።”

“19/ Negotiate and sign air services agreements with Contracting States and Aeronautical Authorities upon delegation by the competent authority and in accordance with the law.”

“፳/ ወደ ኢትዮጵያ እና ከኢትዮጵያ ውጭ መደበኛ በረራ ለሚያደርጉ አየር መንገዶች የክረምትና የበጋ ወቅት የበረራ ፕሮግራሞችን መርምሮ ያጸድቃል።”

“20/ Approve flight schedules both of winter and summer seasons for air lines operating scheduled flight services to and from Ethiopia.”

“፳፩/ በአውሮፕላን ማረፊያ ውስጥና ዙሪያ ያለውን የመሬት አጠቃቀም በተመለከተ ከሚመለከተው አካል ጋር በመማከር ይወሰናል።”

“21/ Determine, in consultation with the appropriate organ, the land use within and around the vicinity of the airports.”

https://chilot.me



“፳፪/ በዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ደረጃ የወጡና አገሪቱ የተቀበለቻቸውን የአቪዬሽን የበረራ ሴፍቲ ደረጃዎችና ተቀባይነት ያላቸውን አሰራሮች መሰረት በማድረግ የተጣጣመ ብሔራዊ የአቪዬሽን ሴፍቲ ፕሮግራም ያወጣል፣ በሚኒስቴሩ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡”

“22/ Establish National Aviation Safety Program in accordance with international and regional aviation safety standards and recommended practices as are practicable and acceptable to Ethiopia; and execute same when approves by the Ministry.”

“፳፫/ በሁሉም የአቪዬሽን አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የአቪዬሽን ሴፍቲ ሥራ አመራር ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡”

“23/ Supervise, follows up and inspect the proper implementation of Aviation Safety Management System in all aviation service providers.”

“፳፬/ ብሔራዊ የአየር ትራንስፖርት ፋሲሊቴሽን ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ ያሻሽላል፣ በሚኒስቴሩ ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡”

“24/ Develop, amend, National Air Transport Facilitation Program and implement same when approved by the Ministry.”

“፳፭/ የኤርፖርቶች አቪዬሽን ፋሲሊቴሽን ፕሮግራም ማስፈጸሚያ መመሪያ ያወጣል፣ ተግባራዊ ያደርጋል.”

“25/ Develop execution manuals for Airport Facilitation Program and Implement same.

“፳፮/ በኮንቬንሽኑ ውስጥ የተካተቱት ደረጃዎችና ተቀባይነት ያላቸው አሰራሮች በአግባቡ ስለመተግበራቸው በኦዲትና ኢንስፔክሽን ያረጋግጣል፣ የአፈጻጸም ሪፖርቱን ለሚኒስቴሩ፣ ለብሔራዊ አየር ትራንስፖርት ፋሲሊቴሽን ኮሚቴ እና ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርስ ያደርጋል፡፡

“26/ Ensure through audit and inspection that standards and accepted practices enshrined in the Convention and properly implemented; and forward the performance reports to the Ministry, the National Air Transport Facilitation Committee and other concerned organs.”

“፳፯/ ከሲቪል አቪዬሽን ፋሲሊቴሽን ጋር የተዛመደ ብሔራዊ የፖሊሲ ሃሳብ ያመነጫል፣ የማሻሻያ ሃሳብ ያቀርባል፣ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

“27/ Initiates National policies concurrent with the civil aviation facilitation; propose recommendations; execute same when approved by the competent organ.”

“፳፰/ የኤርፖርቶች ፋሲሊቴሽን ፕሮግራምን ይመረምራል፣ ያጸድቃል፡፡

“28/ Review and approve Airport Facilitation Program.”

“፳፱/ ከብሄራዊ የአቪዬሽን ሴኪዩሪቲ ፕሮግራም መስፈርቶች ጋር የተጣጣመ የኤርናቪጌሽን አገልግሎትን፣ የአቪዬሽን ሴኪዩሪቲ ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ ይተገብራል፣ ያሻሽላል፡፡

“29/ Consistent with the national aviation security programs, develop, execute, and review air navigation services and aviation security programs.”

“፴/ በሀገሪቱ ውስጥ ተመዝግበው አገልግሎት ለሚሰጡ አየር መንገድ ኦፕሬተሮች እና የበረራ ሰራተኞች ሰርተፊኬት ይሰጣል፡፡

“30/ Issue certificate to all air lines operators and crew members registered in Ethiopia.”

https://chilot.me



፴፩/ ከአቪዬሽን ኢንደስትሪ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ ሥልጠና፣ የምርምር እና የማማከር አገልግሎት ይሰጣል፡፡

፴፪/ የምድር ላይ ድጋፍ አገልግሎት የሚሰጥበትን ሥርዓት ይወስናል፣ ይቆጣጠራል።

፴፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም በቺካጎ ኮንቬንሽን አንቀጽ ፹፫ ቢ.አይ.ኤስ. መሠረት አግባብ ካለው የውጭ ኤሮኖቲካል ባለሥልጣን ጋር በሚደረግ ስምምነት ባለስልጣኑ፡-

ሀ) በኢትዮጵያ ተመዝግቦ በሌላ ሀገር ውስጥ በኪራይ፣ በቻርተር ወይም በሌላ ተመሳሳይ ስምምነት ኦፕሬት የሚያደርግን አውሮፕላን አስመልክቶ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሥራውንና ተግባሩን ለተጠቀሰው ሀገር በሙሉ ወይም በከፊል ያስተላልፋል፡፡

ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ በኪራይ፣ በቻርተር ወይም በሌላ ተመሳሳይ ስምምነት ኦፕሬት የሚደረግ በውጭ ሀገር የተመዘገበ አውሮፕላንን አስመልክቶ የመዝጋቢውን ሀገር የሲቪል አቪዬሽን ባለስልጣን ስራውንና ተግባሩን እንዳስፈላጊነቱ በሙሉ ወይም በከፊል ይቀበላል፡፡

ሐ) የሦስተኛ ወገን ሀገሮች የኃላፊነት ማስተላለፍን በተመለከተ በቺካጎ ኮንቬንሽን አንቀጽ ፹፫ ቢ.አይ.ኤስ. መሰረት ከተፈራረሙና ይህን አንቀጽ በመንግስታቸው አጸድቀው የኃላፊነቱን መተላለፍ ካሳወቁት የኦፕሬተሩን ሀገር ስምምነት ሊቀበለው ይችላል፡፡

፲፬/ ከአዋጁ አንቀጽ ፴፬ ንዑስ አንቀጽ (፬) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተጨምሯል::

"፭/ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ባለስልጣኑ አንድን ኤሮድሮም ኦፕሬተር ለመዝጋት ይችላል:-

ሀ) አየር ማረፊያው አውሮፕላን ለማሳረፍ እና/ወይም ለማስነሳት ብቁ ሆኖ ሳይገኝ፤

"31/ Provide training, research and consulting services in relation to aviation industries."

"32/ Determines the rules under which ground handling services are provided and regulate same."

"33/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of Article 3 and in accordance with article 83 BIS of the Chicago Convention, and based on agreements with the relevant foreign aeronautical authority:

a) The Authority may transfer its duties and functions in whole or in part to another country regarding an aircraft registered in Ethiopia under the Convention and operating in such other state on lease, charter, interchange of aircraft or any similar arrangement.

b) Regarding aircraft registered in another state under the Convention, which is being operated in Ethiopia on lease, charter or any similar arrangement, the Authority may accept the duties and functions, in whole or in part, of the state of registry of the aircraft."

c)The Authority may recognize third party agreements containing responsibilities of the Aeronautical Authorities of State of the Operator in exercising transferred duties and functions provided that the third party States have ratified Article 83 BIS of the Chicago Convention and that it has been informed of the transfer.

14/ The following new Sub-Article (5) is added after Sub-Article (4) of Article 34.

"5/ The Authority may, where the following circumstances occur, order the closure of an aerodrome operator when:

a) The aerodrome is unsuitable for airplanes to land and/or take off;

https://chilot.me



ለ) በባለስልጣኑ ኢንስፔክተር የተገኘው ጉድለት ለአውሮፕላኑ እንቅስቃሴ አዳጋች ሆኖ ሲገኝ፣

ሐ) ያለበትን የሴፍቲ ችግር እንዲያስተካክል በተደጋጋሚ የተሰጠውን ምክረ-ሃሳብ ካላሟላ፡፡"

፲፭/ የአዋጁ አንቀጽ ፴፱ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፡፡

"፩/ ማንኛውም አውሮፕላን አዛዥ ፓይለት የኢትዮጵያን አየር ክልል አቋርጦ ሲበር ወይም በአየር ክልሉ ሲንቀሳቀስ በባለሥልጣኑ የተወሰኑትን የአየር መስመሮች ወይም በአየር ትራፊክ ተቆጣጣሪው የተፈቀዱትን መከተልና ወደተከለከሉ፣ ገደብ ወደተደረገባቸው ወይም አደገኛ ተብለው ወደተሰየሙ ክልሎች ውስጥ ከመግባት መታቀብ አለበት።"

፲፮/ የአዋጁ አንቀጽ ፶ "የአየር ትራፊክ አገልግሎት" የሚለው ርዕስ ተሰርዞ "የኤርናቪጌሽን አገልግሎት" በሚል ተተክቷል፡፡

፲፯/ የአዋጁ አንቀፅ ፶፫ ርዕስ ተሰርዞ "የምስክር ወረቀትና ፈቃድ አስፈላጊነት" በሚል ሐረግ የተተካ ሲሆን በዚሁ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪)፣ (፬) እና (፭) ውስጥ "ኦፕሬሽን ፈቃድ" ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ ‹‹የምስክር ወረቀት ወይም ሌላ ሕጋዊ ማስረጃ›› የሚል ሐረግ ተጨምሯል፡፡

፲፰/ የአዋጁ አንቀጽ ፶፫ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተተክቷል፡፡

"፫/ ባለስልጣኑ የቀረበለትን ማመልከቻ መርምሮ አመልካቹ በዚህ አዋጅና በአዋጁ መሰረት በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ደህንነቱ የተጠበቀ የአውሮፕላን ማረፊያ ኦፕሬሽን ለማካሄድ በሚገባ የተዘጋጀና ብቃት ያለው መሆኑን ካረጋገጠ በኃላ ፍቃዱን፣ የምስክር ወረቀቱን ወይም ሌላ ህጋዊ ማስረጃ ይሰጠዋል፡፡"

b) The findings of the inspector of the Authority confirm that the aerodrome is unsuitable for the movement of an aircraft;

c) It fails,upon successive recommendations, to rectify its safety issues."

15/ Sub-Article (1) of Article 39 is deleted and replaced by the following new Sub-Article (1).

"1/ Any pilot in command of an aircraft crossing or flying in the Ethiopian airspace shall strictly observe the air routes designated by the authority or cleared by the air traffic controller; and shall refrain from flying to or in a non-fly zone; limited flight zone or territories designated as dangerous."

16/ The title of Article 50 of the Proclamation "Air traffic service" is deleted and replaced by the phrase "Air navigation Service".

17/ The title of Article 53 of the proclamation is deleted and replaced by the phrase "Certificate and License Required" and after the phrase "operating license "under Sub-Articles (1), (2), (4) and (5) of Article 53the phrase "Certificate or other legal documents" is added.

18/ Sub-Article (3) of Article 53 is deleted and replaced by the following new Sub-Article (3).

"3/ The Authority shall review and issue license, certificate or other legal documents to the applicant where it finds satisfactorily that the applicant is ready to operate an aerodrome in accordance with this Proclamation, Regulations and Directives issued as per the Proclamation."

https://chilot.me



፲፱/ የአዋጁ አንቀጽ ፶፫ ንዑስ አንቀጽ (፮) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፮) ተተክቷል፡፡

"፮/ ባለስልጣኑ ይህን አዋጅና በአዋጁ መሰረት የወጡ ደንቦችን፣ መመሪያዎችና ትዛዞችን ለማስከበር ማንኛውንም የአውሮፕላን ማረፊያ የኦፕሬሽን ፈቃዱ፣ የምስክር ወረቀቱን ወይም ሌላ ህጋዊ ማስረጃ በዚህ አዋጅ ክፍል ስምንት ድንጋጌዎች መሰረት ማገድ ወይም መሰረዝ ይችላል፡፡"

19/ Sub-Article (6) of Article 53 is deleted and replaced by the following new Sub-Article (6).

"6/ The Authority may, with a view to enforcing the provisions of this Proclamation, Regulations, Directives and orders issued as per the Proclamation, suspend or cancel aerodrome operating license, certificates or other legal documents."

፳/ የአዋጁ አንቀጽ ፷ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሐ) ሥር "የግል አየር ትራንስፖርት ፈቃድ" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "የጠቅላላ አቪዬሽን ኦፕሬሽን ፈቃድ" በሚል ሐረግ ተተክቷል፡፡

20/ The phrase "Private Air Transport License" under Sub-Article (1) paragraph (c) of Article 60 is deleted and replaced by the phrase "General Aviation Operation License."

፳፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፷ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተሽሯል፡፡

21/ Sub-Article (4) of Article 60 is hereby repealed.

፳፪/ የአዋጁ አንቀጽ ፸ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፡፡

22/ Sub-Article (1) of Article 70 is deleted and replaced by the following new Sub-Article (1)

"፩/ ማንኛውም የአውሮፕላን ኦፕሬተር አውሮፕላኑ በበረራ ላይ እያለ በአውሮፕላኑ ወይም በኦፕሬሽኑ ምክንያት ወይም በአውሮፕላኑ ውስጥ ያለ ሰው ወይም እቃ ወይም ከአውሮፕላኑ ጋር የተያያዘ እቃ በመውደቁ ምክንያት በመሬት ላይ ባለ የሶስተኛ ወገን ህይወት፣ አካል ወይም ንብረት ወይም አካባቢ ላይ ለሚደርስ ጉዳት ኃላፊ ይሆናል፡፡"

"1/An airline operator shall be liable for damages caused due to its aircraft or operation, or person in the aircraft, or objects falling from the aircraft, or parts of the aircraft and causing a fatal or physical injury on third party, damages to property or the environment."

፳፫/ የአዋጁ አንቀጽ ፸፪ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ለ) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ (ለ) ተተክቷል፡፡

23/ Sub-Article (1) paragraph (b) of Article 72 is deleted and replaced by the following new Sub-Article (1).

"ለ) በበረራ ላይ መጠቀም የተከለከሉ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎችን ሲጠቀም ቢገኝ፣ ከብር ሃምሳ ሺ በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአንድ ዓመት በማይበልጥ እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡"

"b) Where found using prohibited electronic devices during flight shall be punished with a penalty of not exceeding Fifty Thousand Birr or not exceeding One Year Imprisonment or both."

፳፬/ ከአዋጁ አንቀጽ ፸፪ ንዑስ አንቀጽ (፪) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) ተጨምረዋል።

24/ The following new Sub-Articles (3) and (4) are added after Sub-Article (2) of Article 72.

https://chilot.me



“፫/ ማንኛውም ሰው ሆን ብሎ አውሮፕላን በበረራ ላይ እያለ የሌዘር ጨረራ ወይም ሌላ ማንኛውንም ዓይነት ጨረራ ወደ አውሮፕላን በመልቀቅ እንቅስቃሴ ያወከ፣ አቅጣጫ ያሳተ ወይም ለአደጋ ወይም አጋጣሚ እንዲጋለጥ ያደረገ እንደሆነ እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡”

“3/ Whoever intentionally discharges a lesser emission or other type of radiation towards an aircraft in flight and diverts the navigation of the aircraft from its normal route or exposes the aircraft to an accident or incident shall be punished with a rigorous imprisonment of not exceeding Ten Years.”

“፬/ ማንኛውም ሰው በንዑስ አንቀጽ (፫) ላይ የተመለከተውን ድርጊት በቸልተኝነት የፈጸመ እንደሆነ እስከ አራት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡”

“4/ whoever commits the offense stated under Sub-Article (3) above negligently, the penalty shall be a rigorous imprisonment not exceeding Four Years.”

፳፭/ የአዋጁ አንቀጽ ፸፰ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ተተክቷል፡፡

25/ Sub-Article (1) of Article 78 is deleted and replaced by following new Sub Article (1).

“፩/ የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፵ (፩) ወይም (፪) የተላለፈ ማንኛውም የውጭ አገር ሲቪል አውሮፕላን ኦፕሬተር እስከ አምስት ሚሊየን የኢትዮጵያ ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡”

1/ any foreign civil article operator who violates the provisions of article 40 (1) or (2) of the proclamation shall be liable to fine up to Birr five million.

፳፮/ የአዋጁ አንቀጽ ፸፰ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክቷል፡፡

26/ Sub article (2) of Article 78 is deleted and replaced by the following new sub-Article (2).

“፪/ ከንግድ አየር ትራንስፖርት ውጭ በሆነ ኦፕሬሽን የተሰማራ ማንኛውም የሲቪል አውሮፕላን ኦፕሬተር፣ የአቭዬሽን ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት፣ የአውሮፕላን ጥገና ተቋም፣ የአውሮፕላን ባለቤት ወይም ተከራይ፣ የአቭዬሽን ባለሙያ ወይም በአቭዬሽን ሥርዓት ውስጥ የኃላፊነት ድርሻ ያለው ማንኛውም ሰው የዚህን አዋጅ ድንጋጌ ወይም በዚህ አዋጅ መሰረት የወጣን ደንብ፣ መመሪያ ወይም ትዕዛዝ ተላልፎ ሲገኝ እንደጥፋቱ ክብደት ከብር ሦስት መቶ ሺ በማያንስ እና ከብር አራት መቶ ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፣ የዚህ ዓይነቱ መተላለፍ ቀጣይነት ካለው እያንዳንዱ ቀን እንደተለያየ ጥፋት ይቆጠራል፡፡”

2/ “any civil aircraft operator other than person conducting an operation in commercial air transport, aerodrome operator, aviation training school, aircraft maintenance organization, aircraft owner or hire, or aviation personnel who violate any provision of this proclamation or regulations, directives or orders issued hereunder shall, depending on the gravity of violation, be liable to affine of not less Birr Three Hundred Thousand and not exceeding Birr Four Hundred Thousand”

፳፯/ በአዋጁ አንቀጽ ፸፰ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተተክቷል፡፡

27/ Sub-Article (3) of Article (78) is deleted and replaced by the following new Sub Article (3).

https://chilot.me



"፫/ በንግድ አየር ትራንስፖርት ኦፕሬሽን የተሰማራ ማንኛውም የሲቪል አውሮፕላን ኦፕሬተር የዚህን አዋጅ ድንጋጌ ወይም በዚህ አዋጅ መሰረት የወጣን ደንብ፣ መመሪያ ወይም ትዕዛዝ ተላልፎ ሲገኝ እንደ ጥፋቱ ክብደት ከብር አራት መቶ ሺ በማያንስ እና ከብር አምስት መቶ ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፣ የዚህ ዓይነቱ መተላለፍ ቀጣይነት ካለው እያንዳንዱ ቀን እንደተለያየ ጥፋት ይቆጠራል።"

**፫. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ መጋቢት ፲፭ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

**ሣህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

3/ "any civil aircraft operator conducting an operation in commercial transport who violates any Proclamation or Regulations, Directives or orders issued hereunder shall, depending on the gravity of violation, be liable to a fine not less than Birr Four Hundred Thousand and not exceeding Birr Five Hundred Thousand.

**3. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 24th day of March, 2020

**SAHLEWOREK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**